# THE GOOD END መልካም ፍፃሜ



በወጣቱ ተልዕኮ (አህመድ የሱፍ)

## Presented by Youth-Mission online Amharic Islamic books publishing.

# THE GOOD END

# መልካም ፍፃሜ

በአብዱሏህ ኢብን ሙሐመድ

ትርጉምና ቅንብር በአህመድ የሱፍ

**All right reserved**

© የወጣቱ ተልዕኮ

የወጣቱ ተልዕኮ ኦንላይን እትም 2008

ሰሜን ወሎ ወልዲያ

ahmedyesuf29@gmail.com

+251927790323

http://youth-mission.mobie.in

ሁሉም ሰው ህይወቱ መልካም ፍፃሜ ያገኘለት ዘንድ ይመኛል ያልማል። አብዛሃኛው ወጣቱ ክፍልም ነገን በተስፋ እየጠበቀ ወጣትነቱን ተደስቶበት በማሳለፍ ሃምሳዎቹና ስልሳዎቹ የእድሜ ክልል ላይ ወደ አሏህ እንደሚመለስ ያስባል። ትልቁ ጥያቄ ግን ነገን ስለመኖርህ ዋስትናህ ምንድነው? ነገ የተቃና ሰው እንደምትሆን ምንድነው ማረጋገጫህ? የሚል ነው።

በዚች አነስተኛ መጽሐፍ የመልካም ፍፃሜ ምንነት ፣ ምልክቶቹ ፣ የመጥፎ ፍፃሜ ምንነትና ምልክቶቹ እንዲሁም ወጣቶች ላይ የሚስተዋሉ የተሳሳቱ ግንዛቤዎችና ቁርአናዊ ግሳፄዎች ተዳሰውበታል ያንብቡት!

# መልካም ፍፃሜ

## በአብዱሏህ ኢብን ሙሐመድ

## ትርጉም በአህመድ የሱፍ

### በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

እዝነቱ እያንዳንዱን ነገር ላካበበው እና በሁሉም ነገር ላይ አዋቂ ለሆነው አሏህ ምስጋናና ልቅና ይገባው። ከአሏህ ውጭ በሃቅ ሊያመልኩት የሚገባ አምላክ አለመኖሩንና ለአለም እዝነት ተደርገው የተላኩት ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) የአላህ መልዕክተኛና ባሪያ መሆናቸውን እንመሰክራለን።

አሏህ በቁርአኑ በሱረቱል አንቀቡጥ አንቀፅ 57 ላይ እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 29:57})>=**

**{57} ሁሏም ነፍስ ሞትን ቀማሽ ናት።**

ሞት ምንኛውም ሰው ከሷ ማምለጥ የማይችላት እውነታ ናት። ሆኖም በእያንዳንዱ ቀን ፣ ሰዓት እና ደቂቃ ወደ እሷ ነው የምንቀርበው። በ2007 በወጣው የሲ አይኤ ፍክት ቡክ መሰረት በእያንዳንዱ ደቂቃ ሁለት ሰዎች ይሞታሉ። ይህ በአመት ሲሰላ ደግሞ 57.9 ሚልዮን ሰዎች የሞትን እጣፋንታ ይቀምሳሉ።

ከዚህ በፊት የነበሩ ነገስታቶችና ባለሃብቶች የታሉ? ባንድ ወቅት ቆነጃጅት እና ወይዛዝርት ፣ ታዋቂ ፣ ዝነኛ ፣ ተጽዕኖ ፈጣሪ የነበሩ ሰዎች የታሉ?

ሞት ከዱንያ ወደ አሂራ የሚደረግ ጉዞ እንጅ አደጋ አይደለም። ሆኖም ስለሞት ማስታወሳችን የመፈጠራች አላማ ምን እንደሆነና ከሞት ብኋላ ላለው ህይወት እንድናሰላስልና እንድናስተነትን ያግዘናል።

**=<({አል-ቁርአን 4:78})>=**

**{78} የትም ስፍራ ብትሆኑ በጠነከሩ ህንፃዎች ውስጥ ብትሆኑም እንኳ ሞት ያገኛችኋል።**

አሏሁ አዘወጀል የፈጠረን እሱን በብቸኝነት ከመገዛት አላማ ጋር እንደሆነ በቁርአኑ አሳውቆናል።

**=<({አል-ቀርአን 51:56})>=**

**{56} የሰው ልጅንም ሆነ ኣጋንትን አልፈጠርኳቸውም እኔን ሊገዙኝ ቢሆን እንጅ።**

እንዲሁም በሌላ የቁርአን አያ ሞትና ህይወትን የፈጠረበትን አላማ ሲገልፅ እንዱህ አለ፡-

**=<({አል-ቁርአን 67:2})>=**

**{2} ያ የትኛችሁ ስራው ይበልጥ ያማረ መሆኑን ሊፈትናችሁ ሞትና ህይወትን የፈጠረ ነው። እሱም አሸናፊ መሐሪ ነው።**

ለቅሬ ገንዘብ ስለከፈልን ወይም ደግሞ የምንቀበርበትን ቦታ ስለ ተናዘዝን ለሞት ተዘጋጅተናል ማለት አይቻልም። ይልቁንም በህይወት እያለን የምንፈልገውን ነገር አሟልተናል ነው ልንል የምንችለው። አሏህን መገዛት ማለት በትዕዛዙ መሰረት ህይወትን መምራትና መልካም ስራዎችን መስራት ሲሆን ለሞት መዘጋጀት ማለት ደግሞ ለአኺራ የሚሆነንን መልካም ስራ በመስራት ስንቅ መያዝ ማለት ነው።

ኢባዳ ወይም የአምልኮት ተግባር የሚለው ፅንሰ ሃሳብ በኢስላም ሁሉን አቀፍ እንጅ ለሶላት ወይም ለዱአ ብቻ አይደለም። ስለዚህ አሏህን የሚያስደስት ማንኛውም ተግባር እንደ ኢባዳ ወይም እንደ አምልኮት ተግባር ይቆጠራል። በዚህም መልካም ሰሪ አማኞች ይመነዱበታል።

አንድ ምሳሌ እናንሳ ሁለት ሰዎች ወደ ማያውቁት ሃገር ለመጓዝ ትኬት ቢቆርጡና አንደኛው ከመሄዱ በፊት ስለዛ ሐገር ቋንቋ ፣ ባህል ፣ ስርዓት ቢማርና ሌላኛው ደግሞ እነዚህን ነገሮች ሳይማር ቢቀር ያለምንም ችግር ፣ ያለምንም መጨናነቅና ፍርሃት ብዙም ግራ ሳይጋባ እዛ ሐገር በደስታ የሚኖረው የትኛው ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

አሏህ እንዲህ አይነቱን ሰው ሲገልፅ ነበር በቁርአኑ እንዲህ ያለው፡-

**=<({አል-ቁርአን 23:99-100})>=**

**{99} (ከነሱ መካከል) በአንዳቸው ላይ ሞት በመጣበት ጊዜ ጌታየ ሆይ! መልሰህ ላከኝ ይላል።**

**{100} በተውኩት ነገር በጎን ልሰራ እከጅላለሁና ይላል።**

ጀሃነም የገቡ ሰዎች ጀሃነም ምን እንዳስገባቸው በተጠየቁ ጊዜ የሚሰጡትን መልስ አሏህ በቁርአኑ አስቀምጦታል።

**=<({አል-ቁርአን 74:43-47})>=**

**{43} ከሰጋጆች አልነበርንም ይላሉ።**

**{44} ሚስኪኖችንም አናበላም ነበር።**

**{45} ከዘባራቂዎች ጋር እንዘባርቅ ነበር።**

**{46} በፍርዱ ቀንም እናስተባብል(እንዋሽ) ነበር።**

**{47} ጥርጣሬ የሌለው(ሞት) እስኪመጣብን ጊዜ ድረስ ይላሉ።**

## የመፈጠራችን አላማ

ህይወት በሞት የሚቋጭ ፈተና ነው። ይህ ማለት ከሞት በኋላ ህይወት ወይም አኺራ የለም ለማለት ሳይሆን መልካም ነገሮችን የመስራት እድላችን ይቋረጣል ለማለት እንጅ።

**=<({አል-ቁርአን 23:115})>=**

**{115} ያለምንም አላማ ለጨዋታ የፈጠርናችሁና ወደ እኛ እንደማትመለሱ ታስባላችሁን?**

በዱንያ ህይወት እያንዳንዷ ስራችን ትመዘገባለች አሏህ(ሱ.ወ.ተ) በሱረቱል ካህፍ አንቀጽ 49 ላይ እንዲህ ይላል፡-

=<({አል-ቁርአን 18:49})>=

**{49} መጽሐፉ ይሰጣቸዋል፤ ሙጅሪሞችም በውስጡ በተመዘገበው ነገር ፈሪዎች ሆነው ታያቸዋለህ። ዋ! ጥፋታችን በቁጥር የተመዘገበ ቢሆን እንጅ ትንሽንም ትልቅንም ነገር የማይተው የሆነ ምን አይነት መጽሐፍ ነው ይላሉ። የሰሩትንም ስራ ሁሉ ከፊትለፊታቸው ተቀምጦ ያገኙታል። ጌታህም አንድንም አይበድልም።**

=<({አል-ቁርአን 62:8})>=

**{8} ያ ከእሱ የምትሸሹት ሞት እሱ በእርግጥ ያገኛችኋል። ከዚያም ሩቅንና ቅርቡን አዋቂ ወደ ሆነው ጌታ ትመለሳላችሁ በላቸው።**

እነዚያ በአሏህ የአመኑና መልካም ስራዎችን አጥርተው ለአሏህ ብለው የሰሩ በጀነት ይመነዳሉ።

=<({አል-ቁርአን 36:55-57})>=

**{55} በእርግጥ የጀነት ሰዎች ያን ቀን በአስደሳች ነገሮች ይጨናነቃሉ።**

**{56} እነሱና ሚስቶቻቸው ደስ የሚል ጥላ ውስጥ ሆነው በዝፋኖች ላይም ጋድም ይላሉ።**

**{57} በውስጧም ፍራፍሬዎችና የሚጠይቁት ነገር ሁሉ አላቸው።**

የአሏህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) አሏህ(ሱ.ወ.ተ) አይኖች አይተውት የማያውቁ ጆሮዎች ሰምተውት የማያውቁ የሰው ልጆች ልብ አስቦት የማያውቅ ውብ ነገሮችን ለደጋግ ባሮቼ አዘጋጅቻለሁ ብሏል ብለዋል።

አሏህ የሻለን ሰዎች እሱ ያዘዘንን ነገር ከሰራን የከለከለንን ነገር ከተከለከልን በዱንያ ህይወት የምንደሰትበትን ነገር ሲሰጠን በመጭው አለም ህይወትም ደረጃችነን ከፍ ያደርገዋል። ታዲያ ይህ የሚሆነው እራሳችነን በአሏህ ትዕዛዝ ስር ካደረግንና በአምልኮተ አሏህ ላይ የምንታገል ከሆነ ነው። እንዲሁም መጥፎ ነገሮች ሲገጥሙን መልካም ነገር እንደሚከተል አስበን ትዕግስት የምናደርግ ከሆነና አሏህ በእኛ ላይ ያፈሰሳቸውን ችሮታዎች አስበን የምናመሰግን ከሆነ ነው። አሏህ እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 39:10})>=**

**{10} ለእነዚያ በዚች ዓለም መልካም ለሰሩት መልካም ምንዳ አላቸው። የአሏህ ምድር ሰፊ ናት፤ (ብትቸገሩ ተሰደዱ)። እነዚያ ትግስተኞች የሆኑ ብቻ ምንዳቸውን ሙሉ እንደሆነ ያለ ስሌት ይቀበላሉ በላቸው።**

አሏህ ለኛ ለሰው ልጆች በዚች ዱንያ ከሰጠን ነገሮች ውስጥ አንዱ በህይወት የምንቆይባትን ጊዜ ወይም እድሜያችን ሲሆን ለዘላለማዊው ህይወት ጀነት የሚጠቅመንን ነገር በመስራት በአግባቡ ከተጠቀምንበት ንግዳችን ትርፋማ ይሆናል። ነገርግን ወንጀሎችን እየሰራን ያለ አግባብ ከተጠቀምነውና በአሏህ ላይ አመፀኛ ሁነን እሱን ከተገናኘን ከከሳሪዎች እንሆናለን። ሆኖም ይህ አይነቱ ተግባር ለዘላለም መጥፊያችን ሊሆን ይችላልና የቀብርን ፈተና እና የመጭውን አለም ህይወት አስበን በአሏህ ላይ ማመፅን ልንፈራ ብሎም ከዚህ ተግባር ልንርቅ ይገባል።

አል-ቡኻሪ 11/88-89

ኢብን መስኡድ(ረ.ዐ) እውነተኛ አማኝ በተራራ ጎን ተቀምጦ በእኔ ላይ ይወድቅብኛል ብሎ እንደሚፈራው ወንጀሉንም እንደዚሁ (የሚፈራ) የሚያይ ነው ብለዋል።

የምናምፀውን የአሏህን ታላቅነት ፣ የቀብርን ፈተና ፣ የሂሳቧን ቀን እና ሲራጥን ፣ ጀነትና ጀሃነምን የዘነጋን ስንቶቻችን ነን? ወንጀሎችን እየሰራን ምንም ነገር እንዳልሰራንስ የምናስብ ምን ያህሎቻችን እንሆን? ወንጀላችን ተጠራቅሞ መጥፏያችን ሊሆን እንደሚችል እንደው ትንሽ አናስብም?

አል-ቡኻሪ 11/283

አነስ ኢብኑ ማሊክ(ረ.ዐ) በነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ግዜ እንደ ትልቅ ወንጀል ወይም ሃጢያት የምንቆጥራቸውን ከፀጉር በላይ ያነሱ ስራዎች እንደሆኑ አስባችሁ ትሰሯቸዋላችሁ ብሏል።

አሁን ላይ ያለው እውነታ ይህ ነው! ወንጀል ሰርተን ወንጀል የሰራን አይመስለንም! አንዳንዶቻችነማ የሰራነው ስራ ወንጃል ወይም ሃጢያት እንደሆነ ሲነገረን ስህተታችነን ተቀብለን ስህተታችነን ከማረም ይልቅ የሰራነው ነገር ትክክል ነው ለማለት ሽንጣችነን ገትረን እንሞግታለን። ይባስብሎ አሏህን ፍራ ስንባል በዛው ስራ ላይ እንገፋበታለን። ሃያሉ አሏህ በቁርአኑ እንዲህ ብሏል፡-

**=<({አል-ቁርአን 3:102})>=**

**{102} እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አሏህን ሊፈራ እንደሚገባው ፍሩት። እናም ሙስሊም ሁናችሁ እንጅ እንዳትሞቱ።**

- በሌላ የቁርአን አያ ደግሞ እንዲህ ብሏል፡-

**=<({አል-ቁርአን 15:99})>=**

**{99} እርግጠኛዋ(የማትቀረዋ ሞት) ወደ አንተ እስከትመጣ ድረስ አሏህን ተገዛው።**

ታዲያ የህይወታችነን መልካም ፍፃሜ ለማሳካት አሏህን መፍራት እና እሱንም ብቻ አጥርተን እስከ እለተ ሞታችን ድረስ መገዛት ይኖርብናል። ነገርግን ሲመቸን አሏህ ያዘዘንን ነገር የምንሰራ ሳይመቸን ሲቀር ደግሞ አላህን እያመፅን የምንኖር ከሆነ ፍፃሜያችን ሊበላሽብን ይችላል። ምክኒያቱም አንዳንድ ሰዎች በህይወታቸው ለረዥም ጊዜ አሏህን በመታዘዝ ላይ ሲጥሩና ሲታገሉ ኑረው ከመሞታቸው ከጥቂት ጊዜ በፊት ወንጀል ሰርተው ፣ አሏህን በማመፅ ላይ ሁነው ህይወታቸው በዚህ መንገድ ፍፃሜ አግኝቶ ዘላለማዊው ህይወት የሚበላሽባቸው እንዳሉ የአሏህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) አሳውቀውናልና።

በቡኻሪ 11/417 ላይ በተዘገበው ሐዲስ መሰረት

የጀሃነም ሰዎች የሚሰሯቸውን ስራዎች ሲሰራ የነበረ ሰው በእሱና በጀሃነም መካከል ስንዝር ሲቀር የጀነት ሰዎችን ስራ ሰርቶ ጀነት የሚገባ እንዳለና የጀነት ሰዎችን ስራ ሲሰራ ኖሮ በእሱና በጀነት መካከል ስንዝር ሲቀረው የጀሃነም ሰዎችን ስራ ሰርቶ ጀሃነም የሚገባ እንዳለ የአሏህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) ተናግረዋል።

እኛ የሰው ልጆች ብዙ ጊዜ ዛሬን ከማሰብ ይልቅ ያልመጣውን ነገን እናስቀድማለን። ሆኖም ነገ ስለመኖራችን ፣ እንዴትና መቼ እንደምንሞት ሳናቅና ዋስትና ሳይኖረን ዛሬ ላይ የሰራናቸውን ወንጀሎች አስበን በተውበት ወደ አሏህ ከመመለስ ይልቅ ያልመጣውን ጊዜ(ነገን) እየጠበቅን ተውበት በመከጀል ከወንጀል ላይ ወንጀል እያደራረብን ዛሬን መኖር አቅቶን ያልመጣውን ያለየነውን የነገን ቀን በተስፋ እንኖራለን። ይህ ግን ፈፅሞ ሊያዋጣን አይችልም ምክኒያቱም የት ፣ እንዴትና መቼ እንደምንሞት እናቅምና። ስንቱ ነው በአደጋ ፣ በድንገተኛ ህመም እንዲሁ ሲስቅ ሲጫወት ውሎ አመመኝ ደከመኝ ሳይል በዛው የሚያሸለብ?

ሳኽል ኢብን ሰአድ እንደተረከው አንድ የጦር ሜዳ ላይ ሙስሊሞች ከኩፋሮች ጋር ከተፋለሙ ብኋላ እያንዳንዳቸው ወደ ጦር ካምፓቸው ተመልሱ። በዚህ ጦርነት ከሙስሊም ወታደሮች መካከል ኩፋሮችን እያደነ የሚገልና የሚፋለማቸው ጀግና ነበር። እናም ለረሱል(ሰ.ዐ.ወ) የአሏህ መልዕክተኛ ሆይ! እንደንትና በሃይል የሚፋለም የለም አሏቸው። ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከጀሃነም ነዋሪዎች ውስጥ ነው አሉ። ከመካከላቸው አንዱ ሲፈጥን ፈጥኜ ቀስ ሲልም ቀስ ብየ እከተለዋለሁ አጅበዋለሁም አለ። ያ ጀግና ሰው ቆስሎ ቶሎ ብሎ ለመሞት

ፈለገና የሰይፉን እጄታ መሬት ላይ አድርጎ የሰይፉን ጫፍ በደረቱ መካከል ሰክቶ እራሱን አጠፋ። ሰውየውም ወደ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ተመልሰና የአሏህ መልዕክተኛ መሆናችሁን እመሰክራለሁ አለ። ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ምንድነው? አሉት። ሰውየውም ሙሉ ታሪኩን ነገራቸው።

አንዳንዶቻችን እኛ ካወቅነው እውቀት ውጭ ሌሎች የሚያቁና የኢባዳ ሰዎች ያሉ አይመስሉንም! የአሟሟታችን ሁኔታ ሳናውቅ ሙስሊሞችን በኩፍር እንወነጅላለን። ብዙዎቻችነም ሰፊ የሆነውን የአሏህን እዝነትና ምህረት በመከጀል በአሏህ ላይ እናምፃለን ፣ አሉ የተባሉ ወንጀሎችን እንሰራለን። ዛሬ ዛሬማ በአሏህ ላይ ማመፅ እንደ ፋሽን ተቆጥሮ የስልጣኔ ምልክት ተደርጎ በመወሰድ ላይ ይገኛል። ይባስ ብሎ የሰራነውን ወንጀል እንደ ጀብዱ ቆጥረነው ለሰዎች መንገራችን። አሏህ ከችሮታው የሚሰጠን ፣ የሚያዝንልንና የሚምረን እሱን ስናምፀውና በአመፀኝነታችን ላይ ስንቀጥል አይደለም! አሏህ አመፆኞችን የሚምራቸው የሚያዝንላቸው ይሰሩት ከነበረው መጥፎ ተግባር ወጥተው በተውበት ሙሉ በሙሉ ወደ እሱ የሚመለሱትን ብቻ ነው። ነገሩ ይህ ጠፍቶን አይደለም በራሳችን ላይ ስንቀልድ እንጅ!

- አሏሁ አዘወጀል ሙዕሚን ባሮቹ የእሱን ቅጣት መፍራትንና እሱን በኢህላስ መገዛትን አጣምረው የያዙ እንደሆኑ በቁርአኑ ገልፃል። አሏህ እንዲህ ይላል፡-

**=<({አል-ቁርአን 23:57-61})>=**

**{57} በእርግጥ እነዚያ ጌታቸውን በመፍራት በፍርሃት(በስጋት) የሚኖሩት።**

**{58} እነዚያ በጌታቸው ተአምራቶች የሚያምኑት።**

**{59} እነዚያ በጌታቸው የማያጋሩት።**

**{60} እነዚያ የሚሰጡትን ነገር ወደ ጌታቸው ተመላሾች መሆናቸውን ልቦቻቸው የሚፈሩ ሆነው የሚሰጡት።**

**{61} እነዚያ በመልካም ስራዎች ይጣደፋሉ። እነሱም ለእሷ ቀዳሚዎች ናቸው።**

የምንሞትበት ጊዜ በጣም ቀርቦ ልንሞት በሆነ ጊዜ በአሏህ ላይ ብዙ ተስፋ ሊኖረንና እሱን ለመገናኘት በጉጉት ልንጠባበቅ ይገባል። ምክኒያቱም አሏህን ለመገናኘት በወደድን ጊዜ አሏህም እኛን መገናኘት ይወዳልና።

# መጥፎ ፍፃሜ

## ለህይወታችን መጥፎ ፍፃሜ ምክኒያት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች

### 1ኛ ተውባን ማዘግየት

ሳይፈተንና ወንጀል ሳይሰራ ያለፈ ወይም የሚያልፍ ሰው የለም አንድም ተውበት አድርጎ መጥፎ ስራውን አብሶለታል ወይም ደግሞ ተውባ ሳያደርግ በአመፀኝነቱ ላይ ገፍቶበት አልፏል። ሆኖም በዚህ ጊዜ በተለያየ ነገር ተፈትነን በሆነ ወንጀል ላይ ወድቀን ወይም ከዚህ በፊት ለፈፀምናቸው ወንጀሎች ተውባ ሳናደርግ ነገ ቶብቸ ወደ አሏህ እመለሳለሁ እያልን ተውበትን በመከጀል አሏህን እያመፅን የምንኖር ከሆነ ፍፃሜያችን ላያምር ይችላል። ምክኒያቱም ሞት በእጃችን አይደለምና። ነገ በህይወት ስለመኖራችን ዋስትናችን ምንድነው? ምንም! ይህ ከሆነ ስለ ነገው ተውባ ማሰብ ትተን ስለ ምንኖርበት ጊዜ ዛሬ በማሰብ ተውበት አድርገን ወደ አሏህ መመለስ ይኖርብናል።

**=<({አል-ቁርአን 24:31})>=**

**{31} አማኞች ሆይ! ትድኑ ዘንድ ሁላችሁም ወደ አሏህ በተውበት ተመለሱ።**

አሏህ የነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ወንጀላቸውን ቀድሞ የማረላቸው ቢሆንም እንኳ በቀን 100 ጊዜ የአሏህን ምህረት ይጠይቁ ነበር።

ሙስሊም 2702

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ሰዎች ሆይ! ወደ አሏህ በተውበት ተመለሱ በእርግጥ እኔ በቀን 100 ጊዜ በተውባ ወደ እሱ እመለሳለሁ ብለዋል።

ኢብኑ ማጃ 4250

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከወንጀሉ በተውበት ወደ አሏህ የተመለሰ ሰው ልክ ወንጀል እንዳልፈፀመ ሰው ነው ብለዋል።

ሸይጧን ሊያታልለን ከሚሞክርባቸው ማምታቻዎቹ መካከል አንዱ ተዉባን ማዘግየት ሲሆን ወንጀል በሰራን ጊዜ ተውባ እንዳናደርግ ለማድረግ ተውበት አድርገን ወደ አሏህ የምንመለስበት በቂ ጊዜ እንዳለን ይወተውተናል። እንዲሁ ተውበት ከማድረግ እንድንርቅ ለማድረግ አሁን ወርቃማው የወጣትነት ጊዜ ላይ ነህ ተዝናና ተደሰት ጎደኞችህ አትመለከታቸውም አርባዎቹና ስልሳዎቹ የእድሜ ክልል ላይ ስትደርስ በተውበት ትመለሳለህ። ያኔም ብዙ ግዴታና ሱና የሆኑ ነገሮችንም ትሰራለህ ሲል ሊሰብከን ይሞክራል።

2ኛ ረዥም እድሜ እንደምንኖር ተስፋ ማድረግ

ብዙዎቻችን በተለይ እኛ ወጣቶች እረዥም እድሜ እንደምንኖር በማሰብ የምንሞት አይመስለንም። በተለይ በዚህ ግዜ ትንሹም ትልቁ ስለ ሞት ማሰብ ያቆመ ይመስል እሩጫው ለዱንያና በውስጧ ለያዘችው ነገር ሁኗልና። ለዚህ ምክኒያቱ ረጅም እድሜ እንደምንኖርና ህልማችነን እውን የምናደርግበት ሰፊ ግዜ እንዳለን ማሰባችን ሲሆን ሸይጧን በዚህ በኩል የዱንያን ፍቅር ልባችን ላይ በመዝራት የአሂራን ህይወት ሊያስረሳን ይሞክራል። ስለሞት አናስብም እንዲያውም ስለሞት ሲነሳ ውስጣችን ይረበሻል ምክኒያቱም ፍላጎታችነን እና ምኞታችነን ጥላሸት ይቀባዋል ብለን ስለምንስብ።

ከአኺራ በላይ ዱንያን አብልጠን ከወደድን ምርጫችን እሷ ትሆናለች፤ ሆኖም ስለ አኺራ ረስተን ልፋታችን ፣ ድካማችን ለዱንያና በውስጧ ለያዘቻቸው ነገሮች ይሆናል። ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ሁለት ነገሮችን ስሜትን መከተልን እና እረዥም ተስፋን እፈራላችኋለሁ ብለዋል።

3ኛ እራስን ማጥፋት

በተለያየ ጊዜ ችግርና መከራ ሊፈራረቅብን ወይም ሊደራረብብን ይችላል። ሆኖም ለችግራችን መፍትሄ ትዕግስት ነው። ይህን በማድረጋችንም ትልቅ ምንዳ የሚያስገኝን ቢሆንም አንዳንድ ሰዎች ችግር ሲያጋጥማቸው ወይም ጭንቀት ላይ ሲሆኖ የችግራቸውና የጭንቀታቸው መፍትሄ እራሳቸውን ማጥፋት ይመስላቸዋል። ነገርግን ይህ ተግባር የችግራችን መፍትሄ ሳይሆን የአሏህን ቁጣ በራሳችን ላይ የምናመጣበትና የመጭው አለም ህይወታችነን የምናጠፋበት መንገድ ነው።

# የመልካም ፍፃሜ ምልክቶች

የመልካም ፍፃሜ ምልክቶች በአንድ ሰው ሞት ላይ መታየታቸው የምስራች ሲሆን ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) የመልካም ፍፃሜ ምልክቶች የሆኑ ነገሮችን አሳውቀውናል። ከነዚህ ምልክቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

1 ሊሞቱ ሲሉ የእምነት ምስክርነት ቃል የሆነችውን ከሊመቱ ላኢላሃ ኢለሏህን ማለት።

አቡዳውድ 3116

የአሏህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) የመጨረሻ ቃሉ(ንግግሩ) ላኢላሃ ኢለሏህ (ከአላህ ውጭ በሃቅ ሊያመልኩት የሚገባ አምላክ የለም የሚለው የሆነለት ሰው ጀነት ገባ ብለዋል።

2 በአሏህ መንገድ እየታገሉ እንደ ሰማዕት ሆኖ መሞት። አሏህ እንዲህ ይላል፦

**=<({አል-ቁርአን 3:169})>=**

**{169} እነዚያ በአሏህ መንገድ የታገሉትን እንደ ሙታን አታስቧቸው በእርግጥ እነሱ ከጌታቸው ዘንድ ህያው ናቸው። ስንቅም አላቸው።**

3 በአሏህ መንገድ ለጦርነት እየተዘጋጁ መሞት ወይም ሐጅ እያደረጉ መሞት

በሙስሊምና በአህመድ በተዘገበው ሐዲስ

የአሏህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) በአሏህ መንገድ የተገደለ ሰው ልክ እንደ ሰማዕታን ይቆጠራሉ እናም በአሏህ መንገድ የሞተ ሰው ሰማዕት ነው ብለዋል።

4 በተላላፊ በሽታ ምክኒያት መሞት

አቡዳውድ የሐ.ቁ 4772

አነስ ኢብን ማሊክ እንዳስተላለፈው

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ወረርሽኝ ለእያንዳንዱ ሙስሊም የሰማዕትነት ምክኒያት ነው(በእሱ ምክኒያት ለሞተ ሰው) ብለዋል።

5 በወሊድ ምክኒያት የሞተች ሙስሊማ

ትርሚዚይ 1062 እና ሙስሊም 1915

ኡባዳ ኢብኑ ሳሚት(ረ.ዐ) እንዳስተላለፈው

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከወለደች ብኋላ በወሊድ ምክኒያት በልጇ የሞተች ሴት ልጇ ወደ ጀነት በእትብቱ ይስባታል ብለዋል።

# ማጠቃለያ

ወደ መልካም ፍፃሜ ከሚያመሩን ጎዳናዎች መካከል

1 አላህን በድብቅም ይሁን በግልፅ መፍራትና ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ትተውልን ያለፍትን ቁርአንና ሱናን አጥብቀን መያዝና ለእሱም መታገል ይህ የህይወታችንን ፍፃሜ ሊያሳምሩ ከሚችሉ ነገሮች አንዱ ነው። አሏህ እንዲህ ብሏል፡-

**=<({አል-ቁርአን 3:102})>=**

**{102} እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አሏህ ሊፈራ እንደሚገባው ፍሩት። እናም ሙስሊም ሆናችሁ እንጅ እንዳትሞቱ።**

እኛ ሙስሊሞች ቆሻሻን ወይም እድፍን እንደምንፀየፈው ሁሉ ሃጢያታችነንም እንዲሁ ልንፀየፍ ይገባል። ትልልቅ ወንጀሎችን የምንሰራ ከሆነ ወደ ጀሐነም የሚያመራን ሲሆን ትንንሽ ሃጢያቶችንም መስራት በቀጠልን ቁጥር ወደ ትልቅ ወንጀልነት ይቀየራሉ። ሆኖም ወንጀል ከሰራን ብኋላ ተውበት አድርገን የማንመልስ ከሆነ ልባችን ትበሰብሳለች መመለሻችንም የከፋ ይሆናል።

2 አሏህን ሁሌም ማስተዋስ

ሁሌም አሏህን የምናስታውስ ከሆነና የመጨረሻ ንግግራችን ላኢላሃ ኢለሏህ ከሆነ መጨረሻችን ያምራል። ምክኒያቱም የአሏህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) የመጨረሻ ንግግሩ ላኢላሃ ኢለሏህ የሆነ ሰው ጀነት ገባ ብዋልኗ።

ማንኛውም አይነት አስተያየት ፣ ትችትና ነቀፌታ ካለዎት በኢሜል አድራሻየ ahmedyesuf29@gmail.com ላይ ሊፅፍልኝ ወይም ደግሞ 251927790323 ላይ ሊደወሉልኝ ይችላሉ። የወጣቱ ተልዕኮ ኢስላማዊ መጣጥፎችን ለማግኘት http://youth-mission.mobie.in ይጎብኙ። ጀዛኩሙለህ ኸይረን ከሲረን!